# የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ መስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 330/2013

## Government Employees' Pension Proclamation Implementation Directive No. 330/2013

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
Public Servants' Social Security Agency

ታህሳስ 12፥ 2013

# ማ ው ጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| መግቢያ ........................................................................ | | 2 |
| ክፍል 1 | ጠቅላላ........................................................................ | 2 |
| ክፍል 2 | ስለ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ምዝገባና ማስረጃ አደረጃጀት...................................... | 6 |
| ክፍል 3 | ስለጡረታ ፈንድና መዋጮ አከፋፈል .............. | 9 |
| ክፍል 4 | የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች .... | 16 |
| ክፍል 5 | የልደት ዘመን አያያዝ ..................................... | 24 |
| ክፍል 6 | የአገልግሎት ዘመን አያያዝ .................................. | 28 |
| ክፍል 7 | ለጡረታ አበል አወሳሰን ስለሚያዝ ደመወዝ ......... | 30 |
| ክፍል 8 | የጡረታ አበል ውሣኔና ክፍያ አፈጻጸም ............... | 32 |
| ክፍል 9 | በወኪል አማካኝነት የጡረታ አበል ስለመክፈል ...... | 34 |
| ክፍል 10 | ስለጡረታ አበል ውሳኔ መነሻ ጊዜና ውዝፍ ጡረታ አበል አወሳሰን ......................................................... | 37 |
| ክፍል11 | በጡረታ መብትና ጥቅም ላይ ስለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሳኔ አሰጣጥ .................................................... | 41 |
| ክፍል12 | ልዩ ልዩ ጉዳዮች ............................................... | 45 |

## መ ግ ቢ ያ

ኤጀንሲው የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ለጡረታ ባለመብቶች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስልት መቀየስ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንና ሠራተኞችን ምዝገባና ማስረጃ አደራጅቶ መያዝ የጡረታ አበል ውሳኔ ሥራ በተቀለጠፈ ሁኔታ እንዲፈጸም ስለሚያደርግ፣

የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማስረጃዎችን ለፈጻሚው ግልጽ ማድረግ ስለሚያስፈልግ፣

በተለያዩ ጊዜያት የወጡ መመሪያዎችን ማጠቃለልና ከመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 እና ከመንግስት ሠራተኞች ጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ/907/2007 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ማስተካከል ስለሚገባ፣

በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 60/2/ ለኤጀንሲው በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለው የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ሥራ አፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል።

## ክ ፍ ል አ ን ድ
## ጠ ቅ ላ ላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 330/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1. "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር መሥሪያ ቤት፣ ተቋም ወይም አካል ሲሆን በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መንግስታዊ ተቋማትና የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፡፡

2. " የመንግስት ሠራተኛ " ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም በመንግስት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በመቀጠር በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው የሚሰራ ሰው ሲሆን የመንግስት ተሿሚዎችን፣ የምክር ቤት አባላትን፣ የመከላከያ ሠራዊትንና የፖሊስ አባልን ይጨምራል፡፡

3. "ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ" ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት፣በመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በመንግስት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ውስጥ በጊዜያዊነት ወይም በቁርጥ ሥራ ከ45 ቀናት ላላነሰ ጊዜ በመቀጠር በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለበት የሚከናወን ስራ ሲሆን በቀን ስራ፣በጥዋ ለቀማ፣በሸንኮራ አገዳ ቆረጣ፣ በመከላከያ ሠራዊት እና በፖሊስ አባላት ማሰልጠኛ ተቋም በምግብ አብሳይነት በኮንትራት የሚቀጠሩ ሠራተኞችን እና ሌሎች መሰል በየዓመቱ እየተደጋገሙ የሚከናወኑ ሥራዎችን አይጨምርም፡፡

4. " በመንግስት የሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም " ማለት የማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የመሰረተ ልማትና መሰል ጉዳዮችን ለማስፈጸም ለተወሰነ ጊዜ የሚቋቋምና የሚዘረጋ መንግስታዊ ሥራዎች ሲሆን በውጪ መንግስታት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተራድኦ (ድጋፍ) የሚካሄዱትን መንግስታዊ የልማት ወይም የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

5. " ማስረጃ " ማለት ለምዝገባ፣ ለጡረታ አበል ውሳኔ ወይም ክፍያ ለመፈፀምና የጡረታ ባለመብቱን ማንነት ለማረጋገጥ ወይም መረጃን ወቅታዊ ለማድረግ የሚቀርብ የመንግስት ሠራተኛው እና/ወይም የጡረታ ባለመብት የግል፣ የአገልግሎት፣ የልደት ዘመን የቤተሰብ፣ የደመወዝና ሌሎች አግባብ ያላቸው የጽሁፍ መረጃዎች ናቸው፡፡

6. "የለውጥ ማስረጃ" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የስም፣ የአቋም መቀየር (የአንድ መሥሪያ ቤት ከሌላ ጋር መቀላቀል ወይም መፍረስ)፣ የመንግሥት ሠራተኛው ወይም የጡረታ ባለመብት የግል

ሁኔታ የመቀየር፣ የአገልግሎት፣ የደመወዝ፣ የጋብቻ፣ ፍቺ፣ የልጅ ልደትና የመሳሰሉት ለውጦችን የሚያረጋግጡ ሕጋዊ መረጃዎችና ሰነዶች ናቸው፡፡

7. «ባለመብት» ማለት በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም የጡረታ አበል ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ተተኪ ነው::

8. "ተተኪ" ማለት የሟች የመንግስት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ ሚስት /ባል፣ ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች፣ (አካል ጉዳተኛ ወይም አእምሮ ህመምተኛ ልጅ ሲሆን እድሜው ከ21 ዓመት በታች የሆነ) እና ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሟች ልጃቸው ድጋፍ ይተዳደሩ የነበሩ ወላጆች ሲሆኑ የጉዲፈቻ ልጆችና ወላጆችን ይጨምራል::

9. " የአካል ጉዳተኛ " ማለት በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ምክንያት የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት (ማየት፣ መስማት ወይም መናገር የተሳነው) ጉዳት የደረሰበት ወይም የአዕምሮ ዝግመት ያለበት ሰው ነው፣

10. " ደመወዝ " ማለት ለሥራ ግብርና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ተቀናሽ የሚሆነው (በህመም፣ በዕዳ፣ በዲሲፒሊን ጉድለት በትምህርትና በመሳሰሉት) ሂሳብ ሳይነሳለት ለአንድ የመንግስት ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ሙሉ የወር ደመወዝ ሲሆን የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ፣ የቀን ሥራ ክፍያ፣ ማንኛውንም አበል፣ ጉርሻ ወይም ቦነስ፣ ኮሚሽን፣ማትጊያ፣ የአገልግሎት ክፍያና የመሳሰሉትን አይጨምርም::

11. " አበል" ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል፣የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልን ይጨምራል፡፡

12." ገቢ ሰብሳቢ" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ የክልል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ ኤጀንሲው ውክልና የሰጣቸው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና የክልል የገቢዎች ባለሥልጣን ናቸው፡፡

13. "የጡረታ መዋጮ " ማለት ለመንግስት ሠራተኞች በየወሩ በሚከፈል ደመወዝ ላይ በመቶኛ መጠን እየታሰበ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች በየወሩ እየተሰበሰበ ለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ የሚደረግ ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ ነው፡፡

14. "በሌላ ምክንያት ከሥራ መሰናበት" ማለት ሠራተኛው በሚሰራበት መስሪያ ቤት ስራና ተያያዥ በሆኑ የዲሲፒሊን ጥፋቶች ምክንያት ሳይሆን ለአሰሪው ሳያሳውቅ ከሥራ በመቅረት፣ ከሥራው ጋር ባልተያያዘ ጥፋት ምክንያት በመታሰር፣ በቅነሳ፣ በችሎታ ማነስና በሌሎች መሰል ጉዳዮች ምክንያቶች ሥራ የሚለቅ ወይም የሚተው ሠራተኛን የሚመለከት ነው፡፡

15. በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

16. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 (በአዋጅ ቁ/907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ (2) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በተሸፈኑ የመንግስት ሠራተኞች፣ የጡረታ ባለመብቶች እና አሠሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክ ፍ ል ሁ ለ ት

## ስለ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ምዝገባና ማስረጃ አደረጃጀት

### 4. ስለምዝገባ

1. በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የሚሸፈኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግስት ሠራተኞች መመዝገብ አለባቸው፡፡

2. በጡረታ ዐቅዱ የተሸፈኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግስት ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና የመለያ ቁጥር ይሰጣቸዋል።

3. የመንግስት ሠራተኛው የግብር ከፋይነት የታክስ መለያ ቁጥር (Tax identification number) ያለው ከሆነ ይኸው የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ተደርጎ ይመዘገባል፡፡ ይህም የመለያ ቁጥር አሰጣጥ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ/714/2003 ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የታክስ መለያ ቁጥር ለሌላቸው የመንግሥት ሠራተኞች በኤጀንሲው የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሰጣል፡፡

4. ተመዝግበው የጡረታ መለያ ቁጥር እንዲሰጣቸው ለተደረጉ የመንግሥት ሠራተኞች የዐቅዱ አባልነታቸውን የሚያረጋግጥ " የዐቅድ አባልነት ካርድ" ይሰጣቸዋል።

5. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለመብት ለኤጀንሲው ማስረጃ በሚልክበት ወይም በሚያቀርብበት ጊዜ የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

6. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የተቀጠሩ የመንግሥት ሠራተኞች ምዝገባን በተመለከተ ኤጀንሲው በሚያወጣው ፕሮግራምና የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ይመዘገባሉ።

7. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከወጣ በኋላ የተቋቋሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የተቀጠሩ የመንግሥት ሠራተኞች ምዝገባ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 6 ና 7 በተገለፀው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል::

8. በዚህ ክፍል በዝርዝር በተገለጸው መሠረት የማስረጃ ለውጥ በወቅቱ ለማያቀርብ የመንግሥት ሠራተኛ፣ ባለመብት ወይም ተተኪዎች የሚወሰነው አበል አስቀድሞ በኤጀንሲው ተደራጅቶ በተያዘው መረጃ መሠረት ነው::

## 5. ለምዝገባ ስለሚቀርቡ ማስረጃዎች

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን አዋጅ ወይም ደንብ፣ እያንዳንዱ የመንግሥት ሠራተኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር የመዘገበውን የህይወት ታሪክ ፎርም፣ የተሰጠውን የቅጥር ደብዳቤ እና ተዛማጅ ማስረጃዎችን ለምዝገባ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው በተጨማሪ የመንግሥት ሠራተኞችን ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማስረጃዎች:-

   ሀ. የምዝገባ ቅፅ

   ለ. ጋብቻ ተፈጽሞ ከሆነ ጋብቻን ለመመዝገብ ሥልጣን ካለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

   ሐ. ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላ ልጆች፣ (አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ ህመምተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው 21 ዓመት ያልሞላ ልጅ) ካሉ ስልጣን ካለው አካል የተሰጠ የልደት ሰርተፍኬት:-

   ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

## 6. የማስረጃ ለውጥ

1. በመንግስት ሠራተኛው የግልና የቤተሰብ መረጃ እንዲሁም በመሥሪያ ቤቱ አቋም፣ ስያሜ፣ ወዘተ ላይ ለውጥ ሲኖር በአዋጁ አንቀፅ 6

በዝርዝር በተቀመጠው መሠረት ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀን ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው መገለፅ ይኖርበታል፡፡

2. አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ባለመብት በምዝገባ ማስረጃው ላይ ለውጥ ሲኖር ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀን ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3. የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲፈርስ፣ ሲከፋፈል ወይም ከሌላ መሥሪያ ቤት ጋር ሲቀላቀል፣

   ሀ. ስለመፍረሱ የፈረሰው የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊ ፣

   ለ. ስለመከፋፈሉ ወይም ስለመቀላቀሉ ሠራተኞቹን የተረከበው የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊ ፣

   በ60 ቀን ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣

4. የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ ከተዛወረ ዝውውሩን ያስፈጸመው መንግሥታዊ አካል በ60 ቀን ውስጥ ወደ ግል ስለመዛወሩ ለኤጀንሲው በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## 7. <u>ስለማስረጃዎች አደረጃጀት</u>

1. በኤጀንሲው ተደራጅተው የሚያዙት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱና የመንግስት የሠራተኛው ማስረጃዎች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እና በአንቀጽ 6 የተመለከቱት ናቸው፡፡

2. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሠራተኞቻቸውን የግል ሁኔታ ፣ የአገልግሎት፣ የቅጥር፣ የዝውውር፣ የስንብት ወዘተ የቤተሰብ መረጃዎችን አደራጅቶ የመያዝና ይህንኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 መሠረት በ60 ቀን ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## ክ ፍ ል ሦስት

## ስለ ጡረታ ፈንድና መዋጮ አከፋፈል

### 8. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ

1. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ
   ሀ/ የሲቪል አገልግሎት ጡረታ ፈንድና
   ለ/ የወታደራዊና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ ይኖሩታል።

2. ከሲቪል የመንግሥት ሠራተኞችና አሠሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በየወሩ የሚከፈል የጡረታ መዋጮ ለሲቪል አገልግሎት ጡረታ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል።

3. ከመከላከያ ሠራዊት፣ ከፖሊስ አባላት፣ ከማረሚያ ጥበቃ አባላትና አሰሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በየወሩ የሚከፈል የጡረታ መዋጮ ለወታደራዊና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል።

### 9. ስለጡረታ መዋጮ ክፍያ

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከተቀጠረበት (ከተመደበበት፣ ከተሾመበት) ቀን አንስቶ በየወሩ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 መሠረት፣

   ሀ. ከሐምሌ 1 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ የደመወዙን 5%፣

   ለ. ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ የደመወዙን 6%፣

   ሐ. ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ የደመወዙን 7%፣

   የጡረታ መዋጮ ይከፍላል።

2. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 714/2003 መሠረት ፣

2.1. ለሲቪል የመንግሥት ሠራተኛው በየወሩ የሚከፈለውን ደመወዝ መሠረት በማድረግ የአሠሪው የመንግስት መስሪያ ቤት ድርሻ፣

ሀ. ከሐምሌ 1 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ ለመንግስት ሠራተኛው በየወሩ በሚከፈለው ደመወዝ ላይ 7%፣

ለ. ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ለመንግስት ሠራተኛው በየወሩ በሚከፈለው ደመወዝ ላይ 8%፣

ሐ. ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ለመንግስት ሠራተኛው በየወሩ በሚከፈለው ደመወዝ ላይ 9% እና

መ. ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ለመንግስት ሠራተኛው በየወሩ በሚከፈለው ደመወዝ ላይ 11% ፣

2.2. ለመከላከያ ሠራዊትና ለፖሊስ አባል በየወሩ የሚከፈለውን ደመወዝ መሠረት በማድረግ የአሠሪው የመንግስት መሥሪያ ቤት ድርሻ፡-

ሀ. ከሐምሌ 1 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ የደመወዙን 18%፣

ለ. ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ የደመወዙን 20%፣

ሐ. ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2006 ድረስ የደመወዙን 22% እና

መ. ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ የደመወዙን 25%፣

የጡረታ መዋጮ ይከፍላል፡፡

3. የጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 (በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ) ከመውጣቱ በፊት በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ለተፈጸመ አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የሰራተኛው ድርሻ 7% የአሰሪው መ/ቤት ድርሻ 11% በድምሩ 18% በወቅቱ ይከፈለው የነበረውን የወር ደመወዝ መሰረት በማድረግ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

## 10. የጡረታ መዋጮ የሚከፈልበት ደመወዝ

1. የመንግሥት ሠራተኛውና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ድርሻ የጡረታ መዋጮ የሚከፈለው ለሠራተኛው በየወሩ የሚከፈለውን መደበኛ ደመወዝ መሠረት አድርጎ ነው፡

2. የመንግሥት ሠራተኛው በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ተቀጥሮ የተለያየ ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነ የጡረታ መዋጮ መከፈል ያለበት የመንግስት ሠራተኛው በመረጠው አንድ መስሪያ ቤት በሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ተመስርቶ ይሆናል፡፡ በመንግስት ሠራተኛው ከተመረጠው የመንግስት መስሪያ ቤትና ደመወዝ ውጪ የሚፈጸም አገልግሎትና የሚከፈል ደመወዝ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት አይታሰብም ወይም አይያዝም ፡፡

3. ለሠራተኛው ደመወዝ የሚከፈለው በቀን፣ በሳምንት፣ በአስራ አምስት ቀናት ወይም የተወሰነ ቁርጥ (piece of work) ሥራ ላይ የተመሠረተ ከሆነ የጡረታ መዋጮ የሚከፈለው የወሩን ክፍያ በማዳመር ከተከፈለው ጠቅላላ ደመወዝ ላይ ይሆናል፡፡

## 11. የጡረታ መዋጮ ገቢ ስለማድረግ

1. እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለመንግስት ሠራተኞቹ የሚከፈለውን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን ድርሻ መዋጮ ጨምሮ ደመወዝ ከተከፈለበት ወር መጨረሻ ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ ለክልል መንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን፣ ለክልል ገቢዎች ባለሥልጣን ገቢ ሰብሳቢ አካላት በየወሩ ገቢ ይደረጋል፡፡ እነዚህ የጡረታ መዋጮ ገቢ

ሰብሳቢ አካላትም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(1) ለተገለፀው የፈንድ ሂሳብ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

2. በየወሩ መጨረሻ ለመንግስት ሠራተኞቹ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ የሠራተኛ ድርሻ የጡረታ መዋጮ ሳይቀንስ የቀረ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መዋጮውን ራሱ እንዲከፍል ይደረጋል::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት የሚከፈል የጡረታ መዋጮ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የፌዴራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መዋጮ ሲሆን በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና በክልል መንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አማካይነት ተሰብስቦ ለጡረታ ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡

4. ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም የልማት ድርጅቶች እና የመንግስት ሠራተኞች ወርሃዊ የጡረታ መዋጮ ኤጀንሲው በሚወክላቸው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን ወይም የክልል ገቢዎች ባለሥልጣን ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተሰብስቦ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያ ሳምንት የሥራ ቀናት ለጡረታ ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡

5. የፌደራል መንግሥት የበጀት ድጎማ የሚያደርግላቸው የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ ካላደረጉ ኤጀንሲው ገቢ መሆን የሚገባውን የጡረታ መዋጮ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመግለጽ ድጎማ ከሚደረግላቸው በጀት ላይ ተቀንሶ ለጡረታ ፈንድ ገቢ ማስደረግ ይኖርበታል፡፡

6. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ገቢ ሳያደርግ ከ3 ወር በላይ ያዘገየ ከሆነ ኤጀንሲው ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ባለበጀት ከሆነ መንግሥት ከሚመድብለት በጀት፣ በራሱ ገቢ የሚተዳደር (ባለበጀት ያልሆነ) መስሪያ ቤት ከሆነ በባንክ ካለው አካውንት ላይ ተቀንሶ ገቢ ለማስደረግ ይችላል፡፡

7. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውም የጡረታ መዋጮ የሚከፍል የመንግሥት መሥሪያ ቤት የባንክ አካውንቱን ለኤጀንሲው የማሳወቅና የባንክ አካውንቱ ሲለወጥም ለውጡን በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ የመግለጽ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

8. ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ (ባለበጀት ያልሆኑ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ ገቢ ሳያደረጉ ከ3ወር በላይ የዘገዩ ከሆነ ኤጀንሲው ወይም በኤጀንሲው ውክልና የተሰጠው አካል በቀጥታ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ንብረት ግብር የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮች ሀብት በመያዝና በመሸጥ የግብር አሰባሰብ የሚከናወንበትን ሥርዓት ለመወሰን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ በመከተልና በመሸጥ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

9. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሀልውና በማክተሙ፣ የሰው ኃይል ብዛቱ ከሚፈለገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ ከ25 ዓመት ያላነሰ እድሜው ከ50 ዓመትና በላይ የሆነ መንግሥት ሠራተኛ በጡረታ ሲሰናበት፣

   ሀ. በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽእኖ የመንግሥት ሠራተኛው በሕጉ መሠረት ጡረታ ለመውጣት ለሚቀረው ጊዜ የጡረታ አበሉ ከመወሰኑ በፊት በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ለሠራተኛው በመጨረሻ የተከፈለው የወር ደመወዙን መሰረት በማድረግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 በተዘረዘረው መሠረት በአሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም አካል ለመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

   ለ. የጡረታ መዋጮ ገቢ መሆኑ ሣይረጋገጥና የጡረታ አበል እንዲወሰን መንግሥት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ለሠራተኛው የጡረታ አበል መወሰን አይቻልም፡፡

10. ከኃላፊነት የተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን (አምስት ዓመት) አገልግሎት ፈጽመው ዕድሜአቸው 50 ዓመት በመሙላቱ የዘለቄታ የጡረታ አበል ሲወሰንላቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ላይ እንደተጠቀሰው የሚፈለገው የጡረታ መዋጮ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9/ሀ/እና/10/መሰረት በጡረታ ፈንዱ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ ማካካሻ የጡረታ መዋጮ ገንዘብ የተከፈለበት ጊዜ በሥራ ላይ አገልግሎት እንደተሰጠበት ተቆጥሮ ለጡረታ አበል አወሳሰን ስሌት የሚታሰብበት አይሆንም፡፡

12. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) \እና (8) ቢኖርም ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በራሱ ገቢ የሚተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት በጡረታ አዋጅ ቁ/714/2003 (በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለሰራተኞች የወር ደመወዝ ከተከፈለበት ወር መጨረሻ ቀን አንስቶ የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ገቢ ካላደረገ ለሰራተኞች ደመወዝ ከተከፈለበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በባንክ የማስቀመጫ ሂሳብ የወለድ መጠን ከሚታሰብ ወለድ እና አምስት በመቶ(5%)ቅጣት ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሰረት ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ገቢ ካላደረገ ገቢ ማድረግ ከነበረበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የባንክ ወለድና 5% (አምስት በመቶ) ቅጣት በየወሩ እየጨመረ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 12. የጡረታ መዋጮ ስለሚከፈልበት አገልግሎት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 የተገለፀው ቢኖርም የመንግሥት ሠራተኛው፡-

1. የወር ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግሥት አካል ወይም በሠራተኛ ማህበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት፣

2. በአዋጅ ቁ/714/2003 (በአዋጅ ቁ/907/2007 እንደሻሻለ) አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት በአሁኑ ጊዜ በመንግስት ሥራ ላይ በቋሚነት ተቀጥረው የሚገኙና አዋጅ ቁ/345/95 ከመውጣቱ በፊት በመንግስት መስሪያ ቤት፣ በመንግስት የልማት ድርጅት፣ በመንግስት ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ለተወሰነ ጊዜ (በጊዚያዊነት ወይም በኮንትራት) አገልግሎት የሰጡበት ጊዜ፣

3. በመንግሥት ትዕዛዝ መንግሥት ከሃምሳ በመቶ(50%) በታች ካፒታል ድርሻ በያዘበት ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፣

4. በትምህርት ምክንያት ግማሽ ደመወዝ ለተከፈለበት፣

5. በመንግሥት ውሣኔ በዓለም ዓቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፣

በመንግስት ሠራተኛው ሙሉ የወር ደመወዝ መሠረት የአሠሪ መንግስት መስሪያ ቤቱና ሠራተኛ ድርሻ ጡረታ መዋጮ በአሠሪው ወይም በመንግስት ሠራተኛው መከፈል ይኖርበታል::

## 13. የጡረታ መዋጮ ክፍያ ስለማሳወቅ

እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት:-

1. የራሱንና የመንግስት ሠራተኞቹን ድርሻ የጡረታ መዋጮ መጠን፣
2. በወሩ ውስጥ የተከፈለውን ጠቅላላ የጡረታ መዋጮ መጠን፣
3. በወሩ ውስጥ ለመንግስት ሠራተኞች የተከፈለውን ደመወዝ፣ የክፍያውን ወርና ዓመተ ምህረት በመለየትና
4. የወሩ የጡረታ መዋጮ ገቢ በአለፈው ወር ገቢ ከተደረገው የጡረታ መዋጮ ልዩነት ያለው ከሆነ የልዩነቱን ምክንያት በመግለጽ፣

ክፍያው ከተፈፀመበት ወር ቀጥሎ ባለው እስከ 30ኛው ቀን ድረስ ማስረጃውን ለገቢ ሰብሳቢ አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል::

## 14. የጡረታ መዋጮ ክፍያ መረጃዎችን አደራጅቶ ስለመያዝ

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሠራተኞቹን ስም ዝርዝር፣ በየወሩ የተከፈላቸውን ደመወዝና የጡረታ መዋጮ መረጃ አደራጅቶ የመያዝና በኤጀንሲው ወይም በገቢ ሰብሳቢ አካላት ሲጠየቅ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

2. ገቢ ሰብሳቢ አካላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 እና 14(1) ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች የጡረታ መዋጮ ገቢ ካደረጉ ከአንድ ሳምንት በኋላ ለኤጀንሲው ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

3. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተላለፈለት ማስረጃ መሠረት የሚፈለገውን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረጉን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፡፡

## 15. የጡረታ መዋጮ ገቢ አለመሆን

የመንግስት ሠራተኛውና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ድርሻ የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለበት አገልግሎት ለጡረታ ተግባር አይያዝም።

# ክ ፍ ል  አ ራ ት

## የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች

## 16. ስለማስረጃዎች አቀራረብ

1. የጡረታ አበል የሚወሰነው በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 714/2003 ክፍል ሁለት፣ በአዋጁ አንቀፅ 53 እና በዚህ መመሪያ መሠረት በሚቀርብ ማስረጃ ነው።

2. መረጃዎች የሚቀርቡት ኤጀንሲው በሚያወጣቸው ቅጾችና እንደሁኔታው መረጃውን የሚሰጠው አካል በሚጠቀምበት አሠራር መሠረት ነው።

3. ለጡረታ አበል አወሳሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች ለኤጀንሲው ወይም ለአሰሪ የመንግስት መሥሪያ ቤት በአደራሻ የተጻፈ ካልሆነ በስተቀር "ለሚመለከተው ሁሉ" በሚል የሚቀርብ የአገልግሎትም ሆነ ማንኛውም የምስክር ወረቀት ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

## 17. ለዘለቄታ ጡረታ አበል ጥያቄ መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

### 1. ዕድሜ በመድረሱ ለሚጠየቅ የጡረታ አበል

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ የጡረታ አበል ሲጠየቅ፡-

ሀ. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ለሚቀጠሩ ወይም ለሚመደቡ ሠራተኞች የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ (ማስረጃ ካልተሟላ በፊደል 'ለ' ላይ የተዘረዘሩት እንዲቀርቡ ይደረጋል)፡-

ለ. ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ለተቀጠሩ ወይም ለተመደቡ የመንግስት ሠራተኞች፣

1. የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ፣
2. በመጀመሪያ /ቅድሚያ/ ለሥራ ሲቀጠር የሞላው የሕይወት ታሪክ ቅጽ (በመጀመሪያ ለሥራ ሲቀጠር የሞላው የሥራ መጠየቂያ ወይም የተያዥ መስጫ ቅጽ ከሆነ ይኸው እንዲላክ ይደረጋል)፣
3. የቅጥር ደብዳቤ
4. በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተፈፀመ አገልግሎት ካለ መነሻና መድረሻው የተገለፀበት ለኤጀንሲው እና/ወይም በአሠሪው የመንግሥት መሥሪያ ቤት አድራሻ የተጻፈ የአገልግሎት ማስረጃ፣

መቅረብ ይኖርበታል፡፡

### 2. በጤና ጉድለት ምክንያት ስለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ

1. ከሥራ ጋር ባልተያያዘ የጤና ጉድለት ምክንያት የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 17(1) "ሀ" ወይም "ለ" ከተገለጸው በተጨማሪ ሠራተኛው ደመወዝ የሚያስገኝ ማንኛውንም ሥራ መሥራት የማይችል ለመሆኑ በሕክምና ቦርድ የተረጋገጠበት የምስክር ወረቀት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በአንቀጽ 17(2) (1) የተገለፀው ቢኖርም የመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ የሚያስገኝ ማንኛውንም ሥራ መሥራት እንደማይችል ባይገለጽም፡-

   ሀ. በዓይን ሙሉ በሙሉ ማየት ያለመቻል ወይም ከአገልግሎት ውጪ መሆን፣

ለ. በአካል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሽባ መሆን፣

ሐ. በአካል መጉደል፣ በአእምሮ መታወክና በመሳሰሉት በሽታዎች ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑን ብቻ የሚገልጽ የህክምና ቦርድ ማስረጃ ከቀረበ በዋናው መሥሪያ ቤት በምዝገባና አበል ክፍያ ዳይሬክተር፣ በሪጅኖች እና በቅ/ጽ/ቤቶች ለኃላፊዎች እየቀረበ ይወሰናል፡፡

## 3. በሥራ ላይ በደረስ የአካል ጉዳት ወይም የጤና ጉድለት ምክንያት ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ

1. ለአንድ የመንግስት ሠራተኛ በሥራ ላይ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 17(1)ከተገለጸው በተጨማሪ:-

    ሀ. ሲቪል የመንግስት ሠራተኛው በሥራ ላይ አደጋ በደረሰበት በ30/ሰላሳ/ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው መሥሪያ ቤት የተገለጸበት የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ፣

    ለ. እንደሁኔታው የፖሊስ ሪፖርት፣

    ሐ. ስለደረሰው የአካል ጉዳት መጠንና ደመወዝ ለሚያስገኝ ማንኛ ውም ሥራ ብቁ ያለመሆኑ የተረጋገጠበት በሕክምና ቦርድ የተሰጠ የምስክር ወረቀት፣

    መ. ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን በፊት ባለው ወር የተከፈለውን የወር ደመወዝ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ፣

    መቅረብ ይኖርበታል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3/1/ሀ/ የተጠቀሰው ቢኖርም ሠራተኛው በስራ ላይ እያለ ከሥራው ጋር በተያያዘ በደረሰበት አደጋ ምክንያት በሞት መለየቱ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከተረጋገጠ የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ ከ30 ቀን በኋላ ቢቀርብም ተቀባይነት ይኖረዋል::

3. ከሥራ ጋር በተያያዘ የጤና ጉድለት /የሙያ በሽታ/ ምክንያት ለሚጠየቅ ጡረታ አበል የሚቀርብ ማስረጃ ዓይነት ኤጀንሲው በሚያወጣው የሙያ በሽታ ሠንጠረዥ መመሪያ ይወሰናል::

4. <u>በራስ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከስራ ማቋረጥ ምክንያት ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ</u>

ሀ. የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከሥራ በመሰናበቱ የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1) ከተገለጸው በተጨማሪ ከሥራ ያቋረጠበት ምክንያት የሚገልጽ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ " ሀ " መሠረት በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ የመንግሥት ሠራተኛ ከ25 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ያለው ከሆነ በሕግ የተወሰነ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ የጡረታ አበል ይወሰንለታል፡፡

ሐ. በአዋጅ ቁ/714/2003 (በአዋጅ ቁ/907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማሻሻያ አዋጁ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱ ከ10 ዓመት ያላነሰ 25 ዓመት ያልሞላ ከሆነ ዕድሜው በሕግ የተወሰነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ የአገልግሎት የጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

መ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ " ለ " የተገለፀው ቢኖርም ከሚያከናውነው ስራ ጋር በተያያዘ የዲስፒሊን ጉድለት ወይም ከሚሰራበት መሥሪያ ቤት ሥራ ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊትና በማንኛውም ጥፋት ምክንያት ከሥራው የተሰናበተ መሆኑ ከተረጋገጠ ዕድሜው 60 ዓመት ከመሙላቱ በፊት የጡረታ አበል ሊወሰንለት አይችልም፡፡

ሠ. በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሰረት ዕድሜው በሕግ ከተወሰነው የጡረታ መውጫ በፊት (በ25 ዓመት አገልግሎት በ55 ዕድሜ) በራስ ፍቃድ የአገልግሎት የጡረታ አበል የተወሰነለት ባለመብት እንደገና በመቀጠር የፈጸመው አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተዳምሮ አበል የሚወሰንለት ዕድሜው በሕግ የተወሰነው የመጦሪያ ዕድሜ (60 ዓመት) ሲደርስ ብቻ ነው፡፡

ረ. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ/907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም በፊት ከሃያ ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በዕድሜና በጤና ጉድለት ሳይሆን በራስ ፈቃድ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ከሥራ ለተሰናበተ የመንግስት ሠራተኛ የሚከፈል የጡረታ አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይኖርም፡፡

## 5. የከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎችን በተመለከተ ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ፡

ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በተመለከተ የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን (አምስት ዓመት) አገልግሎት፣

ለ. ዕድሜው ከ50 ዓመት ያላነሰ መሆኑን፣

የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 6. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የሚሠራበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሕልውና በማክተሙ፣ የሰው ኃይል ብዛት ከሚፈለገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ ከሥራ እንዲሰናበት ከተደረገና በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 17(1) ከተገለፀው በተጨማሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጡረታ እንዲገለል የተሰጠ ውሣኔ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

# 18. የአንድ ጊዜ ክፍያ ጥያቄ

## 1. የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት

ሀ. የመንግሥት ሠራተኛው ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ ለጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ወይም፡-

ለ. ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ ለሚያስገኝ ለማንኛውም ሥራ ብቁ ባለመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት፣

ሐ. ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን (አምስት ዓመት) ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ከኃላፊነት በመነሳቱ ምክንያት ዳረጎት ከተጠየቀ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1)ና እንደሁኔታው 17(2) የተገለጹት ማስረጃዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2. የሥራ ላይ ጉዳት ዳረጎት

በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት የጉዳት ዳረጎት ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(3)(1) የተገለፀው ማስረጃ መቅረብ ያለበት ሲሆን በህክምና ቦርድ የተረጋገጠው የጉዳት መጠንም ከ10% ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ዳረጎት ስሌቱም ጉዳት ከደረሰበት በፊት ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዝ 47% X 60 X በሠራተኛው ላይ በደረሰበት ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ይሆናል፡፡

## 3. የጉዳት ዳረጎት

በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 38/1/ መሠረት የጉዳት ዳረጎት የሚከፈለው በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው መሰረት በአሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት የጉዳት ካሳ ወይም የመድን ክፍያ ያልተከፈለው ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## 4. የጡረታ መዋጮ ተመላሽ የማይደረግ ስለመሆኑ

በአዋጅ ቁ/714/2003 (በአዋጅ ቁ/907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 27 መሰረት የመንግስት ሰራተኛ አገልግሎት በማናቸውም ምክንያት ቢቋረጥ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይደረግም፡፡ ሆኖም ሠራተኛው ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ በፈጸመው አገልግሎት ምክንያት የተከፈለ የጡረታ መዋጮ የሠራተኛው ድርሻ ብቻ ታስቦ ተመላሽ ሊደረግለት ይችላል፡፡

# 19. የተተኪዎች አበል ጥያቄ

## 1. የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል ጥያቄ

የሚስት ወይም የባል የጡረታ አበል ሲጠየቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1) እና እንደሁኔታው በአንቀጽ 17(3) ከተዘረዘረው በተጨማሪ፡-

ሀ. ሟች የመንግስት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ በሕይወት ያለ ለኤጀንሲው መሥሪያ ቤት ያቀረበውና ተመዝግቦ የተያዘ የጋብቻ ማስረጃ የሌለ ከሆነ በፍ/ቤት የተሰጠ የሚስትነት (ባልነት) ማረጋገጫ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ. ጋብቻን በሚመለከት የቀረበው ማስረጃ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ሌላ ጋብቻ ስለመፈጸሙ ወይም ፍቺ ስለመኖሩ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ማድረግ ይቻላል፡፡

ሐ. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) እና (ለ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ/5/1967 አንቀጽ 34 መሰረት ከሶስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኖበት የጡረታ አበል የማግኘት መብቱን ያጣ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የጡረታ አበሉ የተቋረጠበት ባለመብት በሞት የተለየ ከሆነ የጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ/907/2007 ጸድቆ በስራ ላይ ከዋለበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ የተተኪው ጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የተገለጸውን የጡረታ አበል ለመወሰን አስቀድሞ ተተኪ ሚስት ወይም ባል ጋብቻ መፈጸም አለመፈጸማቸውን እንዲሁም ተተኪ ልጆች በህይወት ስለመኖራቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የማሻሻያ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ዕድሜያቸው 18 ዓመት (አካል ጉዳተኛ 21 ዓመት) ለሞላቸው ተተኪ ልጆች የሚወሰን አበል አይኖርም፡፡

## 2. የልጅ ጡረታ አበል ጥያቄ

የልጅ የጡረታ አበል ሲጠየቅ እንደሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1) እና 17(3) ከተገለጹት

በተጨማሪ፣

ሀ. ሟቹ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ በሕይወት እያለ ለኤጀንሲው መሥሪያ ቤት የልጅ የልደት ምስክር ወረቀት አቅርቦ

ያላስመዘገበ ከሆነ በፍርድ ቤት የተሰጠ የልጅነት ማረጋገጫ ማስረጃ፣

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መሠረት አስቀድሞ ለኤጀንሲው ቀርቦ በተመዘገበ ማስረጃ መሰረት የጡረታ አበል ለሚወሰንላቸው ልጆች በሕይወት ስለመኖራቸው ከሚኖሩበት ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በምስክሮች የተረጋገጠ ማስረጃ፣

ሐ. የፍርድ ቤት ማስረጃ ሳይቀርብ በኤጀንሲው ምዝገባ መሠረት የጡረታ አበል ለሚወሰንላቸው ልጆች አበል የሚከፈለው ዋናው ባለመብት በሕይወት እያለ ባስመዘገበው የልጅ እናት ወይም አባት አማካይነት ይሆናል:: ሆኖም በፍርድ ቤት ማስረጃ መሠረት አበል የሚወሰን ከሆነ በፍርድ ቤት በተሾመ የሞግዚት ማስረጃ ላይ በተገለጸው የሞግዚት ማስረጃ ፣

መ. የጉዲፈቻ ልጅ ሲሆን የጉድፈቻ ውሉ ጉድፈቻ አድራጊው በህይወት እያለ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀበት ማስረጃ፣

መቅረብ ይኖርበታል::

### 3. የወላጅ ጡረታ አበል ጥያቄ

የወላጆች ጡረታ አበል ሲጠየቅ እንደሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1) እና 17(3) ከተገለጹት በተጨማሪ:-

1. በፍርድ ቤት የተሰጠ የወላጅነት ማረጋገጫ፣
2. የጉዲፈቻ ወላጅ ሲሆን የጉድፈቻ ውሉ የጉድፈቻ ልጁ በሕይወት እያለ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀበት ማስረጃ፣
3. በሟች ልጃቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሚደረግ ድጋፍ /ዕርዳታ / ይተዳደሩ የነበረ ለመሆኑ እና ወላጅ እናት ወይም አባት ልጃቸው በሞተበት/ችበት/ ጊዜ ስለነበራቸው የመተዳደሪያ ገቢ፣ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

### 4. ባለመብቱ መሞቱን ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ማስረጃ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19(1)(ሀ) እና (19)(2)(ሀ) መሠረት አስቀድሞ በተመዘገበ መረጃ መሠረት የጡረታ አበል ሲወሰን የመንግሥት ሠራተኛው ስለመሞቱ ከአሠሪው የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ባለመብቱ በጡረታ

ከተገለለ በኃላ የሞተ ከሆነ ስለመሞቱ ከቀበሌ አስተዳደር ወይም ከሕክምና ተቋም ወይም የሞት ማስረጃ ለመስጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 20. የተተኪዎች የአንድ ጊዜ ክፍያ ጥያቄ

1. ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ለፈጸመና የሥራ ውሉ ሳይቋረጥ ለሞተ የመንግስት ሠራተኛ የሚስት/ባል/ እና የልጆች ዳረጎት ሲጠየቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1)፣19(1) እና 19(2) የተገለጹት ማስረጃዎች መቅረብ አለባቸው፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሟች የጡረታ ባለመብት በህይወት እያለ ያልተቀበለው ውዝፍ የጡረታ አበል በጡረታ አዋጅ አንቀጽ 41/1/ እና 42/1/ መሰረት እየታሰበ ለተተኪዎች ይከፈላል፡፡ ሆኖም ሟች ተተኪ ሚስትና ልጆች ከሌሉት በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ አንቀጽ 43 መሰረት ለወላጆች እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

3. ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የሟች ልጅ ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ ህመምተኛ ዕድሜው ከ21 ዓመት በላይ ከሆነ ምንም ዓይነት የጡረታ አበል ሊከፈለው አይችልም፡፡

4. የተተኪዎች የአንድ ጊዜ የዳረጎት ክፍያ የሚፈጸመው ለሚስት/ ለባል/ እና ወይም ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች፣ የአካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ከሆነ ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች ብቻ ነው፡፡

# ክ ፍ ል አ ም ስ ት
# የልደት ዘመን አያያዝ

## 21. ለጡረታ ተግባር ስለሚያዝ የልደት ዘመን

1. ለጡረታ ተግባር የሚያዘው የልደት ዘመን የመንግሥት ሠራተኛው በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ ወይም አገልግሎቱ

እንዲያዝ በተደረገ መሥሪያ ቤት ሲቀጠር ለመጀመሪያ ጊዜ /በቅድሚያ/ የመዘገበው የልደት ቀን፣ ወርና፣ዓ.ም ወይም ዕድሜ ነው::

2. ለጡረታ ተግባር የሚያዘው ዕድሜ በቅድሚያ በተሞላ የሥራ መጠየቂያ ወይም የሕይወት ታሪክ መግለጫ ቅጽ ወይም ከ1968 ዓ/ም በፊት የተሞላ የተያዥ መስጫ ቅጽ ወይም የምዝገባ ቅጽ ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን ነው::

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው በማይኖርበት ጊዜ በመሥሪያ ቤቱ በመረጃነት የተያዘና የልደት ዘመን የተገለጸበት ከተዘጋጀበት ዘመን አኳያ ቅድሚያ ያለው ማስረጃ ተይዞ ይሠራል::

## 22. <u>የልደት ቀን፣ ወርና ዓ.ም ስለመዘገበ ሠራተኛ</u>

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የተወለደበት ቀን፣ ወርና ፣ዓ.ም ተመዝግቦ ከተገኘ ይኸው የልደት ዘመን ተይዞ ይሰራል::

## 23. <u>የልደት ዘመን ብቻ ስለመዘገበ ሠራተኛ</u>

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ:-

1. ቀንና ወር ሳይጠቅስ የልደት ዘመን ብቻ መዝግቦ ከተገኘ በመሥሪያ ቤቱ በተያዘና በተከታታይ ከተመዘገቡት ዘመኑ የተለየ ቢሆንም ቅድሚያ ባለው የልደት ዘመን በተገለፀበት ማስረጃ ላይ የተመዘገበ ቀንና ወር ይያዛል:: ወርና ቀን ያልተጠቀሰ ከሆነ በተመዘገበው ልደት ዘመን ላይ በጡረታ አዋጅ የተወሰነውን የመጦሪያ ዕድሜ በመደመር በሚገኘው ዘመን መጨረሻ ወር እንደሁኔታው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሆነ ነሐሴ 30 ቀን ወይም እ.ኤ.አ. ከሆነ ታህሳስ 30 ቀን ዕድሜው ለመጦሪያ እንደደረሰ ተቆጥሮ ከሚቀጥለው ዓመት መጀመሪያ ወር አንስቶ በጡረታ ይገለላል::

2. ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን መወለዱ ከተመዘገበ ዕድሜው ለጡረታ የሚደርሰው ከተወለደበት ቀን በፊት ባለው ወር መጨረሻ ቀን ነው::

3. ወር በገባ ከ2 እስከ 30 ካሉት ቀናት መወለዱን ወይም ወርና ዓ.ም ብቻ የመዘገበ ከሆነ በጡረታ የሚገለለው ከተወለደበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል::

## 24. ዕድሜ ብቻ ስለመዘገበ የመንግሥት ሠራተኛ

የመንግስት ሠራተኛው በቅድሚያ በተሞላው ቅጽ ላይ ዕድሜውን ብቻ የመዘገበ ከሆነ ቅጹ ከተሞላበት ቀን፣ወርና ዓ.ም ላይ ዕድሜው ተቀንሶ ልደት ዘመኑ ይያዛል፡፡ በቅጹ ላይ ቀንና ወር ካልተገለጸ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23(1) መሠረት ይፈጸማል፡፡

## 25. የተለያየ የልደት ዘመንና ዕድሜ ስለመዘገበ ሠራተኛ

1. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ቅድሚያ ባለው ዕድሜና የልደት ዘመን እንዲመዘገብ በሚጋብዘው ቅጽ ላይ የተለያየ የልደት ዘመንና ዕድሜ የመዘገበ ከሆነ በተከታታይ ከተሞላው ቅጽ ላይ በአንዱ ዓመተ ምህረቱን ወይም ዕድሜውን በመድገም ከመዘገበ ይኸው በቅድሚያ የተመዘገበው ዓመተ ምህረት ወይም ዕድሜ ይያዛል፡፡

2. በተከታታይ በተመዘገቡት የልደት ዘመን መረጃዎች ላይ በቅድሚያ ተመዝግቦ የነበረው ዕድሜ ወይም ዓ.ም ያልተደገመ ከሆነ በቅድሚያ በተመዘገበው ዘመን ላይ ወርና ቀን ተገልጸ ሲገኝ ይኸው ዘመን ይያዛል፣ በዘመኑ ላይ ቀንና ወር ያልተጠቀሰ ከሆነ ዕድሜው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 መሠረት እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

## 26. በመጀመሪያ ሲቀጠር የልደት ዘመኑን ስላልመዘገበ ሠራተኛ

አንድ የመንግስት ሠራተኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በሞላው ቅጽ ላይ የልደት ዘመኑ ያልተመዘገበ ከሆነ ወይም ቅጽ ያልሞላ ከሆነ በተከታታይ ከተሞሉት ቅጾች መካከል ቅድሚያ ባለው ቅጽ ላይ የተመዘገበው የልደት ዘመን ይያዛል፡፡ ሠራተኛው ቅጽ ያልሞላ ከሆነ በአሠሪው መሥሪያ ቤት በተያዘ የልደት ዘመን የተገለጸበት ቅድሚያ ባለው ማስረጃ ወይም ይህ በማይኖርበት ጊዜ የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ ላይ የተገለጸ የልደት ዘመን ተይዞ ይሰራል፡፡

## 27. የልጆች ልደት ዘመን አያያዝ

1. ለልጆች የሚያዘው የልደት ዘመን የጡረታ ባለመብቱ በሕይወት እያለ በኤጀንሲው መሥሪያ ቤት ያስመዘገበው የልደት ዘመን ነው፡፡

2. መንግስት ሠራተኛው በህይወት እያለ የልጅ ዕድሜ ያላስመዘገበ ከሆነ በአሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት በተያዘ ልደት ዘመን የተገለጸበት ቅድሚያ ባለው ማስረጃ ላይ የተመዘገበ ልደት ዘመን ወይም ልጁ የተወለደው ሠራተኛው

ከሞተ በኋላ ከሆነ በፍ/ቤት ውሳኔ የተገለጸው የልጅ ልደት ዘመን ይያዛል:: ይህ ከሌለ ቅድሚያ ባለው ሌላ ማስረጃ ላይ የተመዘገቡ የልደት ዘመን ይያዛል::

3. በማስረጃው ላይ የልጅ እድሜ ብቻ ከተጠቀሰ መረጃው ከተዘጋጀበት ወይም ፍ/ቤት ካመለከቱበት ወርና ዓ.ም ላይ በማቀናነስ ይያዛል:: በማስረጃው ላይ ወር ካልተገለጸ በአበል መጠየቂያ ቅጽ ላይ የተመዘገበው ወር ይያዛል::

## 28. ስለልደት ዘመን የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች

1. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሞላው ቅጽ ላይ:-

   ሀ/ በመሥሪያ ቤቱ በመረጃነት ተይዞ የሚሰራበት ከሆነ የኃላፊ ፊርማ ባይኖረውም፣

   ለ/ የሠራተኛውን ፊርማ በማይጋብዝና በጊዜው የሚሰራበት ሆኖ የሚመለከተው ኃላፊ የፈረመበት ከሆነ፣

   ሐ/ የሠራተኛውንም ሆነ የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊ ፊርማ የማይጋብዝ በጊዜው ማስረጃነቱ ታምኖበት የሚሠራበትና ቅድሚያ ያለው ሆኖ ከተገኘ፣

   ተቀባይነት ይኖረዋል::

2. የመንግሥት ሠራተኛው በአንድ ቀን በተሞሉ ቅጾች ማለት:-

   ሀ. በሥራ መጠየቂያ፣
   ለ. በሕይወት ታሪክ ፎርም፣
   ሐ. በቅጽ ጡም 1 ( በምዝገባ ቅጽ)፣
   መ. ከ1968 ዓ.ም በፊት በተሞላ የተያዥ መስጫ ፎርም፣
   ላይ የተለያየ የልደት ዘመን መዝግቦ ከተገኘ ከ " ሀ" እስከ " መ " ከተገለጹት እንደቅደም ተከተላቸው ቅድሚያ የተሰጠ የልደት ዘመኑ ይያዛል::

3. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ ያለ በሞላው ቅድሚያ ባለው ቅጽ ወይም አስቀድሞ በአሠሪው መሥሪያ ቤት በተያዘ የልደት ማስረጃ መሠረት ወደ ጡረታ እንዲመደብ በሚደረግበት ጊዜ አስቀድሞ የታወቀውን የልደት ዘመን ለማስተባበል ሲባል የሚያቀርበው ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም::

## ክ ፍ ል ስ ድ ስ ት

## የአገልግሎት ዘመን አያያዝ

### 29. ለጡረታ ተግባር ስለሚያዝ አገልግሎት ዘመን

1. ለአንድ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያዘው የጡረታ መዋጮ እየተከፈለበት በመንግሥት መሥሪያ ቤት በቋሚነት ወይም በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ወይም በተወሰነ ጊዜ ወይም በተወሰነ ሥራ የተፈጸመ የአገልግሎት ዘመን ነው፡፡

2. የአንድ መንግሥት ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመንግሥት ሠራተኛነት ከተቀጠረበት ወይም ከተመደበበት ወይም ከተሾመበት ቀን አንስቶ በሙሉ ዓመት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም የሚከተሉት አገልግሎቶች ለጡረታ ተግባር ይያዛሉ፡፡

    ሀ. የመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግሥት አካል ወይም በሠራተኛ ማህበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

    ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት መዋጮ የተከፈለበት አገልግሎት፣

    ሐ. በመንግሥት ትዕዛዝ መንግሥት /ከ50%/ በታች የካፒታል ድርሻ በያዘባቸው ድርጅቶች አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

    መ. የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሆነ ወይም ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር ከተዋሃደ የመንግሥት ፕሮጀክት ጋር አብሮ በመዛወር የመንግሥት ሠራተኛ ለሆነ በጊዜያዊነት በፕሮጀክቱ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

    ሠ. ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ተራዝሞለት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

    ረ. የጡረታ መውጫ ዕድሜ በመድረሱ አበል ከተወሰነለት በኋላ በመንግሥት ውሳኔ ወደ ሥራ ተመልሶ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ሰ. የደመወዝ ክፍያ ሣይቋረጥ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ፣

ሸ. በመንግሥት ውሣኔ በዓለም አቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሣለፈው ጊዜ፣

ቀ. ከጡረታ መውጫ እድሜ በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት በመመረጥ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

በ. በፌዴራል መንግሥት ወይም በክልል መንግሥት ተሹሞ ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በላይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ተ. የተጠራቀመ ፕሮቪደንት ፈንድ ያለው የግል ድርጅት ሠራተኛ ወደ መንግስት መሥሪያ ቤት ከተዛወረና በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 10 መሠረት ያለውንና ከጡረታ መዋጮ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የተጠራቀመ ፕሮቪደንት ፈንድ ለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ ካደረገ በግል ድርጅት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ቸ. የመንግሥት ሠራተኛው በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 በተሸፈነ የግል ድርጅት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ኀ. የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፍሎት ከመንግስት ስራ የተሰናበተ የመንግስት ሰራተኛ ወይም የግል ድርጅት ሰራተኛ እንደገና በመንግስት ስራ ከተቀጠረ ወይም ከተመደበ የወሰደውን ዳረጎት መልሶ ገቢ ያደረገበት አገልግሎት ፣

ነ. የጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከመጽናቱ በፊት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በመንግስት ሠራተኛነት ከተቀጠረ ወይም ከተመደበ የወሰደውን የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጭምር መልሶ ገቢ ያደረገበት አገልግሎት፣

ለጡረታ ተግባር ይያዘል፡፡

## 30. ከመቀጠሪያ ዕድሜ በፊት ስለተፈፀመ አገልግሎት

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ ከተወሰነው የመቀጠሪያ ዕድሜ በፊት ተቀጥሮ አገልግሎት የፈፀመ ከሆነ ዕድሜው 14 ዓመት ከሞላ ጊዜ ጀምሮ የፈፀመው አገልግሎት ይታሰብለታል::

## ክፍል ሰባት

## ለጡረታ አበል አወሳሰን ስለሚያዝ ደመወዝ

## 31. ለጡረታ አበል ስሌት ስለሚያዝ ደመወዝ

1. ለአገልግሎት ጡረታ አበል ስሌት የሚያዘው የመንግሥት ሠራተኛው መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ የተከፈለው አማካይ ደመወዝ ነው:: በመጨረሻ በተፈጸመ አገልግሎት መሰረት የተከፈለው ደመወዝ ሦስት ተከታታይ ዓመታት(36 ወራት) የማይሞላ ሆኖ ሲገኝ ቀሪውን ወደ ኋላ በመሄድ ቀደም ሲል አገልግሎት በሰጠባቸው ጊዜ ከተከፈለው የወር ደመወዝ እንዲሟላ ይደረጋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም መዋቅራዊ አደረጃጀትና የተጠና የደመወዝ ስኬል በሌለበት የግል ድርጅት በተቀጠረ በ3 ዓመት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በጡረታ የሚገለል ሰራተኛ በጡረታ ከሚገለልበት ወር 3 ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ይከፈለው ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ በ25% የሚበልጥ ዓመታዊ አማካይ የደመወዝ ጭማሪ ያገኘ እንደሆነ በየዓመቱ እስከ 25% ያለው የደመወዝ ጭማሪ ብቻ በደመወዙ ላይ ተዳምሮ የ3 ዓመት አማካይ የወር ደመወዙ ተይዞ እንዲታሰብ ይደረጋል::

3. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተወሰነ በኋላ በሥራ ላይ ቆይቶ የጡረታ አበል ከተጠየቀለት የጡረታ አበሉ የሚሰላው ለሥራ በቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠበት ወደ ኋላ የተከፈለውን የ36 ወራት አማካይ ደመወዝ በመያዝ ነው::

4. በህመም ምክንያት በስራ ላይ ለማይገኝ የመንግስት ሰራተኛ የደመወዝ አከፋፈል በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ/515/1999 አንቀጽ 42/3/

የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም ከሥራ ጋር ባልተያያዘ የጤና ጉድለት ምክንያት ከሥራ ለሚሠናበት የመንግሥት ሠራተኛ የሰላሳ ስድስት (36)ወር አማካኝ ደመወዝ የሚያዘው ሲከፈለው በነበረው ሙሉ የወር ደመወዝ መሠረት ነው፡፡

5. በሥራ ላይ ለደረሰ ጉዳት አበል ስሌት የሚያዘው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት የተከፈለ ደመወዝ ነው፡፡ ሆኖም ሠራተኛው በአገልግሎቱ የሚያገኘው አበል የተሻለ ሆኖ ሲገኝ አማካይ ደመወዝ በአገልግሎት አበል አወሳሰን መሠረት ይያዛል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ለመንግሥት ሠራተኛው ለመጀመሪያ 10 ዓመት ለፈጸመው አገልግሎት የ36 ወር አማካይ ደመወዙ 30% (ሰላሣ በመቶ) ይታሰባል፡፡

7. በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 714/2003 መሠረት ከ10 ዓመት በላይ ለተፈጸመ አገልግሎት፣

   7.1. ለሲቪል አገልግሎት ለእያንዳንዱ ዓመት አገልግሎት በአማካይ ደመወዙ፣

      ሀ. ከሐምሌ 1 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ 1.15%፣

      ለ. ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ 1.19%፣

      ሐ. ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ 1.22%

      መ. ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ 1.25%፣

      ሠ. አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ላገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል መጨረሻ ይከፈለው የነበረው የሰላሳ ስድስት (36) ወር አማካኝ ደመወዝ 15% ሲሆን ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን በላይ ላገለገበት ለእያንዳንዱ ዓመት 1.125%፣ እየተጨመረ ይታሰባል፡፡

   7.2. ለመከላከያ ሠራዊትና ለፖሊስ አገልግሎት ለእያንዳንዱ ዓመት በአማካይ ደመወዙ፡-

      ሀ. ከሐምሌ 1 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ 1.53%፣

ለ. ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ 1.58%፣

ሐ. ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ 1.62%

መ. ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ 1.65%

እየተጨመረ ይታሰባል፣

## 32. ለዳረጎት ስሌት ስለሚያዝ ደመወዝ

1. የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት አበል ለመወሰን የሚያዘው የመንግስት ሠራተኛው በዕድሜ ወይም በጤና ጉድለት ከሥራ ከሚሰናበትበት ወር በፊት የተከፈለውን የወር ደመወዝ በመያዝ ነው።

2. የጉዳት ዳረጎት የሚወሰነው በመንግስት ሠራተኛው ላይ ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ባለው ወር የተከፈለውን ደመወዝ በመያዝ ነው።

# ክ ፍ ል ስ ም ን ት

## የጡረታ አበል ውሳኔና ክፍያ አፈጻጸም

## 33. ስለጡረታ አበል ውሳኔ

በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት የሚከፈል ማንኛውም የጡረታ አበል ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በኤጀንሲው ነው።

## 34. የጡረታ አበል ውሳኔ ስለማሳወቅ

ማንኛውም ዓይነት አበል ከተወሰነ በኋላ፦

ሀ. የጡረታ አበሉ ዓይነትና መጠን፣

ለ. አበሉ መከፈል የሚጀምርበት ጊዜና ቦታ ፣

ለአበል ተቀባዩ መገለጽ ይኖርበታል።

## 35. የጡረታ አበል ክፍያ

1. የጡረታ አበል ለባለመብቱ በየወሩ ይከፈላል። ሆኖም በጡረታ ባለመብቱ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ በየ3 ወይም በየ6 ወሩ ሊከፈለው ይችላል።

2. የዳረጎት አበል ለአንድ ጊዜ ብቻ ለባለመብቱ ይከፈላል።

## 36. የጡረታ አበል ስለሚታገድበት/ ስለሚቋረጥበት/ሁኔታ

የጡረታ አበል ክፍያ የሚታገደው ወይም የሚቋረጠው

1. ባለመብቱ ከሞተበት፣
2. ዋናው ባለመብት ዜግነቱን ከቀየረ ዜግነቱን ከቀየረበት ጊዜ ጀምሮ
3. የባል ጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለች ሚስት ዕድሜዋ ከ45 ዓመት በታች ከሆነ ወይም የሚስት ጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባል ዕድሜው ከ50 ዓመት በታች ከሆነ ጋብቻ ከፈፀመችበት (ከፈጸመበት) ጊዜ፣
4. የልጅ ዕድሜ 18 ዓመት (አካል ጉዳተኛ ወይም አእምሮ ህመምተኛ ከሆነ 21 ዓመት) ከሞላበት ጊዜ፣
5. በተከታታይ አበል ሳይወስድ ሦስት(3) ወር ከሞላበት ጊዜ ወይም በባለመብቱ ጥያቄ በየ6 ወሩ እንዲከፈል የተወሰነለት ባለመብት ይኸው ጊዜ ከተጠናቀቀበት ከሚቀጥለው ወር፣
6. አበሉ የተወሰነው ያለአግባብ መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ፣ ቀጥሎ ካለው ወር ፣

አንስቶ ይታገዳል / ይቋረጣል/::

7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አካል ጉዳተኛ መሆኗን ወይም መሆኑን እውቅና ካለው የህክምና ተቋም ማስረጃ ለምታቀርብ ወይም ለሚያቀርብ ሚስት ወይም ባል ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
8. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) አፈጻጸም የልደት ዘመን ለማረጋገጥ በመንግስት ሠራተኛው ወይም በጡረታ ባለመብቱ ወይም በተተኪው በተለያየ ጊዜያት በምዝገባ ፣በጡረታ አበል መጠየቂያ እና ልዩ ልዩ ቅጾች የተመዘገበን የልደት ዘመን ወይም ባለመብቱ በትምህርት ላይ በነበረ ጊዜ የተመዘገበ ልደት ፣ከጋብቻ በፊት የተሰጠ የልደት ፣የቀበሌ ወይም የፍርድ ቤት እና የመሳሰሉትን ማስረጃዎች ማገናዘብና ማረጋገጥ ያስፈልጋል::
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 270/1994 ከወጣ በኋላ ዜግነቱን ቀይሮ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ያቀረበ የጡረታ መብቱን ሊያገኝ ይችላል፡፡

## 37. የዕዳ አከፋፈል

1. ለማንኛውም ባለመብት የጡረታ አበል ያለአግባብ የተከፈለው ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 55(3) መሠረት የመመለስ ግዴታ ይኖርበታል። ባለመብቱ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ከሆነ ዕዳው ከሚከፈለው አበል ላይ 1/3/ሲሦው/ እየተቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል።

2. ለባለመብቱ መከፈል ያለበት የአንድ ጊዜ ክፍያ(ውዝፍ) የአበል ክፍያ ካለ ለዕዳው እንዲተካ ተደርጎ ቀሪው ይከፈለዋል። ሆኖም የአንድ ጊዜ ክፍያው ዕዳውን የማይሸፍን ከሆነ በየወሩ ከሚከፈለው አበል ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በየወሩ እየተቀነሰ ገቢ ይደረጋል።

3. ባለመብቱ በህይወት እያለ በፍርድ ቤት ክርክር ከጡረታ አበሉ ላይ ለሚስት(ለባል) ወይም ለልጅ ቀለብ እየተቀነሰ እንዲከፈል ውሳኔ ከተሰጠ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ የሚቻለው ባለመብቱ የጡረታ አበሉን በየወሩ እየቀረበ ሲቀበል ብቻ ነው።

# ክ ፍ ል ዘ ጠ ኝ
# በወኪል አማካይነት የጡረታ አበል ስለመክፈል

## 38. የጡረታ አበል በውክልና ስለሚከፈልበት ሁኔታ

አንድ የጡረታ ባለመብት፡-

1. በእርጅና፣
2. በሕመም፣
3. ውጪ አገር በመሄድ፣
4. በትምህርት፣
5. በእስራት፣
6. ሥራ ተቀጥሮ ወይም የራሱን ሥራ በማቋቋሙ ከክፍያ ጣቢያ ርቆ በመሄዱ፣
7. በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ፣

ምክንያት የጡረታ አበሉን ተከታትሎ ለማስወሰን ወይም ቀርቦ ለመቀበል በማይችልበት ሁኔታ ላይ ከሆነ ጉዳዩን በወኪል አማካይነት ለማስፈጸም ወይም አበሉን በወኪል አማካይነት ለመቀበል ይችላል።

## 39. የውክልና አፈጻጸም

ውክልና የሚፈፀመው በኤጀንሲው (በዋና መ/ቤት፣ በሪጅን ጽ/ቤቶች፣ በቅ/ጽ/ቤቶች፣ በመስክ ጽ/ቤቶች ወይም እንደሁኔታው በክፍያ ጣቢያዎች) ይሆናል፣ ሆኖም፡-

1. ባለመብቱ ውክልና ለመስጠት ሥልጣን በተሰጠው አካል አማካይነት ውክልና ሰጥቶ ውጪ አገር ከሄደ በኋላ የውክልና ማስረጃው ሲቀርብ፣

2. ባለመብቱ ውክልና ሳይሰጥ ውጪ አገር ከሄደ በኋላ በሚኖርበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ውክልና ሰጥቶ ማስረጃውን ሲያቀርብ፣

3. ባለመብቱ በማረሚያ ቤት የሚገኝ ከሆነ ውክልናው በማረሚያ ቤቱ ሀላፊ ተረጋግጦ ማስረጃው ሲቀርብ፣

4. ባለመብቱ በህክምና ተቋም ተኝቶ ህክምና እየተከታተለ ስለመሆኑ ከህክምና ተቋሙ የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ፣

5. ከኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ርቀው በሚገኙ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑና በጤና ጉድለት ወይም በእርጅና ምክንያት አበላቸውን በየወሩ ቀርበው ለመቀበል ላልቻሉ ባለመብቶች በሚኖሩበት አካባቢ ውክልና ለመስጠት ሥልጣን ባለው አካል የተፈፀመ የውክልና ማስረጃ ሲቀርብ፡፡

ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## 40. ውክልና ለመፈጸም ስለሚቀርብ ማስረጃ

1. ባለመብቱ የውክልና ጥያቄ ያቀረበው፡-

   ሀ. በጤና ጉድለት ምክንያት ከሆነ የጤና ጉድለቱን የሚገልጽ የሕክምና ማስረጃ፣

   ለ. በሥራ ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢው ርቆ በመሄዱ ምክንያት ከሆነ ሥራ ስለመቀጠሩ ከቀጣሪው ወይም በግል ሥራ ተሠማርቶ ከሆነ ከቀበሌ የተሰጠ ማስረጃ፣

   ሐ. በትምህርት ምክንያት ከሆነ ከሚማርበት የትምህርት ተቋም የተሰጠ ማስረጃ፣

   መ. ወደ ውጪ አገር በመሄድ ምክንያት ከሆነ የባለመብቱ ፓስፖርትና መግቢያ ቪዛ ፎቶ ኮፒ፣

ሠ. በመታሰሩ ምክንያት ከሆነ ከማረሚያ ቤቱ የተሰጠ ማስረጃ ::

ረ. የኢትዮጵያን ዜግነት በቀየረበት ሁኔታ ከሆነ የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጪ አገር ዜጋ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብ ውክልና ይሰጣል::

2. ባለመብቱ ውክልና ሳይሰጥ ወደ ውጪ አገር የሄደ ከሆነ በአለበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት አማካይነት ውክልናው የተፈፀመበትን ማስረጃ ከፓስፖርት ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ያስፈልጋል፣

3. በእርጅና ወይም ማስረጃ ሊቀርብበት በማይቻልበት የጤና ጉድለት ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አበሉን ቀርቦ ለመቀበል ለማይችል ባለመብት በሚመለከተው የሪጅን ወይም የቅ/ጽ/ቤት ሀላፊ እንደሁኔታው እየታየ ውክልና ይፈጸማል::

## 41. የባለመብቱን በሕይወት መኖር ስለማረጋገጥ

1. በእርጅና፣ በጤና ጉድለት እና በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በኃላፊዎች ውሳኔ በወኪል አማካይነት አበል እንዲከፈለው የተደረገ ባለመብት በሕይወት ስለመኖሩ በየሦስት ወሩ በአካል ከቀረበ ወይም ከሚኖርበት አካባቢ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ማስረጃ ሲያቀርብ ውክልናው ይራዘምለታል:: ከኤጀንሲው ጽ/ቤት ርቀው በሚገኙ ቦታዎች የሚኖሩ ባለመብቶች ማስረጃውን ለከፋይ ተቋማት ያቀረቡ በተቋማቱ በኩል ወደ ኤጀንሲው መተላለፍ ይኖርበታል:: ሆኖም በዓመት አንድ ጊዜ ባለመብቱ በአካል ቀርቦ መታየት አለበት::

2. ውጪ አገር የሚኖር ባለመብት በየዓመቱ ከሚኖርበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ወይም በሚኖርበት አገር ሕግና ደንብ መሰረት ውክልናውን አድሶ ማስረጃ ሲልክ ውክልናው ይራዘማል:: ሆኖም በየጊዜው ፓስፖርቱ የታደሰበትን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል::

3. በትምህርት ምክንያት በወኪል አማካይነት አበል የሚከፈለው ባለመብት በዓመት አንድ ጊዜ በአካል ቀርቦ መታየት አለበት:: ባለመብቱ በእስር ምክንያት በወኪል አማካይነት አበል የሚከፈለው ከሆነ በዓመት አንድ ጊዜ ከታሰረበት ማረሚያ ቤት በሕይወት ስለመኖሩ ማስረጃ ሲቀርብ ውክልናው ይራዘማል::

4. የጡረታ ባለመብቱን በሕይወት መኖር ለማረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) በተጠቀሱት መሠረት የሚቀርብ ማስረጃ፣

ሀ. ከተጠቀሰው ጊዜ አንድ ወር በፊት ለኤጀንሲው መሥሪያ ቤት ከደረሰ ወይም ወካይ በአካል ቀርቦ ከታየ የውክልናው ጊዜ ከሚያልቅበት ጊዜ አንስቶ እንደሁኔታው ለሦስት ወራት ወይም ለአንድ ዓመት፣

ለ. የተጠቀሰው ጊዜ ከአለፈ በኋላ እንደ ውክልናው ዓይነት በሶስት ወራት ወይም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ከደረሰ ወይም በአካል ቀርቦ ከታየ ውዝፉ ተከፍሎ ማስረጃው ከደረሰበት ወይም ወካይ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ክፍያው እንደሁኔታው ለሦስት ወራት ወይም ለአንድ ዓመት ጊዜ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## ክ ፍ ል  አ ሥ ር

## ስለጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜና ውዝፍ ጡረታ አበል አወሳሰን

### 42. የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜ አወሳሰን

አንድ የመንግስት ሠራተኛ፡-

1. ወደ ጡረታ ከሚሄድበት ወር ቀጥሎ ባለው የሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የጡረታ አበል ጥያቄ ለኤጀንሲው መሥሪያ ቤት ከቀረበ የጡረታ አበሉ ወደ ጡረታ ከሚሄድበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ ይከፈለዋል፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 49(2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ጡረታ ከሚሄድበት ወር ሦስት ዓመት በኋላ የጡረታ አበል ጥያቄ ከቀረበ ጡረታ አበሉ ክፍያ መነሻ ጊዜ ጥያቄው ለኤጀንሲው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡

3. በጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 907/2007 መሰረት በጽኑ እስራት ምክንያት የጡረታ አበሉ የተፈቀደለት ባለመብት የአበሉ መነሻ ጊዜ አዋጁ ከጸናበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ ይሆናል፡፡ ሆኖም የማሻሻያ አዋጁ ከፀናበት ቀን አንስቶ ከሦስት ዓመት በኋላ ጥያቄው ከቀረበ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 43. የተተኪዎች የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜ አወሳሰን

1. የሚስት ወይም የባል ወይም የወላጅ ጡረታ አበል ጥያቄ ባለመብቱ በሞተ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ከቀረበ ባለመብቱ ከሞተበት ከሚቀጥለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ አበል ይከፈላል፡፡

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም አንድ ባለመብት በሞተ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባል ወይም ሚስት ወይም ወላጅ መብቱን ለማስከበር ለፍ/ቤት አመልክቶ ከፍ/ቤት ሥነ ሥነሥርዓት ጋር በተያያዘ ምክንያት ጉዳዩ ከዘገየና በፍ/ቤት ውሳኔ በተሰጠ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄው ለኤጀንሲው ከቀረበ አበሉ ባለመብቱ ከሞተበት ከሚቀጥው ወር አንስቶ ይከፈላል፡፡

3. ሚስት ወይም ባል ወይም ወላጅ መብቱን ለማስከበር ባለመብቱ ከሞተ ሦስት ዓመት በኋላ ለፍ/ቤት አመልክቶ በፍ/ቤት ውሳኔ በተሰጠ ሦሥት ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄው ለኤጀንሲው ከቀረበ ለፍ/ቤት ካመለከተበት ወር አንስቶ አበል ይከፈላል፡፡

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 49(2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚስት ወይም የባል ወይም የወላጅ የጡረታ አበል ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ከተጠቀሱት ጊዜ ውጪ ከቀረበ ማስረጃው ለኤጀንሲው ከቀረበበት ወር አንስቶ አበል ይከፈላል፡፡

5. ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ አበሉ ባለመብቱ ከሞተበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ ይከፈላቸዋል፡፡

6. የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ 714/2003 ከመውጣቱ በፊት ዕድሜአቸው 18 ዓመት የሞላቸው አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ ህመምተኛ የሆኑ ልጆች ዕድሜአቸው ከ21 ዓመት በታች ቢሆንም እንደገና አበል የማግኘት መብት የላቸውም፡፡

7. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) ና አንቀጽ 44 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለመብቱ በመጥፋቱ ምክንያት ለተተኪ

የጡረታ አበል የሚወሰነው ፍ/ቤት የመጥፋት ውሳኔ ከሰጠበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ ነው።

## 44. በባለመብቱ ምክንያት ዘግይቶ ስለሚቀርብ ማስረጃ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 42 እና 43 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመደበኛ ባለመብቶችም ሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል ጥያቄ ለኤጀንሲው መ/ቤት ቀርቦ ባለመብቱ ማስረጃ እንዲያቀርብ ተገልጾለት እያለ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባለማቅረቡ ምክንያት አበል ሳይወሰንለት ከቆየ የአበሉ መነሻ ጊዜ ማስረጃው ተሟልቶ ከቀረበበት ወር አንስቶ ይሆናል።

## 45. ተሻሽሎ ስለሚወሰን ጡረታ አበል ክፍያ ውሳኔ መነሻ ጊዜ

1. የጡረታ አበል ሲወሰን ያልቀረበ የአገልግሎት፣ የደመወዝና ሌላ ማስረጃ ዘግይቶ ሲቀርብ የጡረታ አበሉ እንደ ማስረጃው አቀራረብ እየታየ ከአንቀጽ 42 እስከ 44 በተገለጸው መሰረት ተሻሽሎ ይወሰናል።

2. በጽኑ እስራት ምክንያት አገልግሎቱ ተቀንሶ የጡረታ አበል የተወሰነለት ባለመብት የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ/714/2003 (በአዋጅ ቁ/907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ አገልግሎቱ ተይዞ አበል ተሻሽሎ ይወሰንለታል፡፡

## 46. ስለውዝፍ ጡረታ አበል አወሳሰንና አከፋፈል

አንድ የጡረታ ባለመብት አበል ተወስኖለት እያለ፡-

1. እስከ ሦስት ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ ውዝፍ አበሉ እንዲከፈለው ከጠየቀ አበሉን መቀበል ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ፡
2. ከሦስት ዓመት በላይ አበሉን ሳይቀበል ቆይቶ ውዝፍ አበሉ እንዲከፈለው ጥያቄ ሲያቀርብ ካመለከተበት ወር አንስቶ ይከፈለዋል።

## 47. የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜና የውዝፍ አበል አወሳሰን የሥልጣን ወሰን፡-

እስከ ሦስት ዓመት ያለ ውዝፍ በሥራ ሂደቱ የውሣኔና ክፍያ ሠራተኛ ይወሰናል። ሆኖም በፍ/ብሔር ሕግ ቁ/1793 ፊደል (ሐ) እና (መ) መሰረት እንደ መሬት

መናወጥ፣ ማዕበል፣ መቅሰፍትና ጦርነት የመሳሰሉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሦስት ዓመት በላይ ውዝፍ እና የክፍያ መነሻ ጊዜ ጥያቄ ሲቀርብ እንደሁኔታው በሥራ ሂደቱ ዳይሬክተር፣ በሪጅኑ ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ይወሰናል::

## 48.የአገልግሎት ክፍያ

አንድ የጡረታ ባለመብት የጡረታ አበሉን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ያልተቀበለና የክፍያ ጥያቄ ካቀረበ በድጋሚ አበል ለማዘጋጀት የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፣ የክፍያው መጠንም በኤጀንሲው ይወሰናል::

## 49.ስለ ይርጋ ጊዜ አፈጻጸም

1.ቀጥሎ ከተገለፀው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ የጡረታ አበል ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል::

ሀ. የጡረታ አበል ጥያቄ ሳይቀርብ ወይም የጡረታ አበል ተወስኖ እያለ ባለመብቱ ሳይቀበል ከሦስት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ከቆየ፣

ለ. የልጅ የጡረታ አበል ጥያቄ እድሜው 18 ዓመት ከሞላ ከሦስት ዓመት በኋላ ከቀረበ፣

ሐ. የዳረጎት አበል ጥያቄ ጥቅሙን ለማግኘት ከሚቻልበት ቀን ወርና ዓ/ም አንስቶ ከሦሥት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ከቆየ፣

2.በሚከተሉት ምክንያት የባከነ ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር አይታሰብም፣

ሀ. ባለመብትነትን ለማረጋገጥ የተጀመረ የፍርድ ቤት ሥነ ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ የወሰደው ጊዜ፣

ለ. ማንኛውም አሠሪ መሥሪያ ቤት መረጃ የማስተላለፍ ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ያለፈ ጊዜ፣

ሐ. ኤጀንሲው የቀረበለትን የክፍያ ጥያቄ መርምሮ ለመወሰን የወሰደው ጊዜ፣

መ. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1793 ፊደል (ሐ) እና (መ) መሠረት እንደ መሬት መናወጥ፣ ማዕበል፣ መቅሰፍትና ጦርነት በመሳሰሉት ከባለመብቱ አቅም በላይና ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ያለፈ ጊዜ ፣

3.የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መጠቀም ከሚቻልበት ከሚቀጥለው ቀን አንስቶ ይሆናል፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## በጡረታ መብትና ጥቅም ላይ ስለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሣኔ አሰጣጥ

### 50. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1. ማንኛውም ባለመብት የጡረታ መብትና ጥቅምን በሚመለከት በኤጀንሲው ባለሙያ በተሰጠ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ከሆነ ቅሬታውን፦
   ሀ. ውሣኔ የተሰጠው በዋናመሥሪያ ቤት ከሆነ ለምዝገባና አበል ክፍያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣
   ለ በሪጅኑ ወይም በቅ/ጽ/ቤቶች ከሆነ ለሪጅኑ ወይም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል።
   ሐ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ለ/ የተጠቀሱት ዳይሬክተሮች ወይም ኃላፊዎች የባለሙያውን ውሳኔ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ለማፅደቅ ይችላሉ፡፡
2. ባለመብቱ በምዝገባና አበል ክፍያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ በሪጅኑ ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሲኖረው በዳይሬክቶሬቱ፣ በሪጅኑ ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል አድራሻውን ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በማድረግ የይግባኝ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታው የቀረበለት ዳይሬክቶሬት፣ የሪጅን ጽ/ቤት ወይም የቅ/ጽ/ቤት ቅሬታውን ከመግለጫ ጋር ለጡረታ ጉዳዮች ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ያስተላልፋል፡፡

3. ማንኛውም ቅሬታ ወይም አቤቱታ የሚቀርብባቸው ጉዳዮች ጡረተኛው በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በሪጅን ጽ/ቤቶች ወይም በቅ/ጽ/ቤቶች በሚገኙ የሥራ ሂደቶች ወይም አስተባባሪዎች ውሣኔ በተሰጠ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይግባኙ ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይቀርባል።

4. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ብሎ የሚያምን

ወገን ጉባኤው ውሳኔ በሰጠ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

## 51. የውሣኔ አሰጣጥ የጊዜ ገደብን በተመለከተ

ማስረጃ ለማሰባሰብ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ለቀረበው ቅሬታ ውሳኔ የሚሰጠው፡-

ሀ. በምዝገባና የአበል ክፍያ ዳይሬክቶሬት፣ በሪጅን ጽ/ቤት ወይም በቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ሲሆን ቅሬታው በቀረበ በሁለት የሥራ ቀናት፣

ለ. በጡረታ ጉዳዮች ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ሲሆን ለቅሬታ አጣሪው በቀረበ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

## 52. የጡረታ ጉዳዮች ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ አመሰራረትና አባላት

1. በዋናው መ/ቤት የምዝገባና አበል ክፍያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ በሪጅን ጽ/ቤት ወይም በቅ/ጽ/ቤት ሀላፊዎች በተሰጡ ጡረታ ነክ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ከመተላለፋቸው በፊት የሚመረምር የጡረታ ጉዳዮች ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡
2. ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በዋናው ዳይሬክተር የሚመደብ ሰብሳቢ፣ አባላትና ፀሐፊ ይኖሩታል፡፡
3. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት ብዛት እንደአስፈላጊነቱ በዋና ዳይሬክተሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 53. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው፡-

1. በዋናው መ/ቤት የምዝገባና አበል ክፍያ ዳይሬክቶሬት፣ በሪጅን ጽ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ የማጣራት ሥራ ያከናውናል፡፡ በዳይሬክተሮችና በጽ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ ሲያገኘው ቅሬታውን በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡
2. ውሣኔ የሚሰጠው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅንና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

3. በቀረበው ቅሬታ ላይ ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት እንዲችል ተጨማሪ ማስረጃዎችን ሊያስቀርብ እና አመልካቾችን ወይም የአሠሪ መ/ቤት ኃላፊዎችን አስቀርቦ ሊያነጋግር ይችላል፡፡

4. ስለሥራው አፈጻጸም በየጊዜው ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 54. የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

1. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በሳምንት አንድ ቀን ይሰበሰባል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ሰብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው ውሣኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፣ ድምፅ እኩል ለዕኩል በሚሆንበት ጊዜ በሰብሳቢው የተደገፈው ሀሳብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
4. በሃሳብ የተለየ አባል ልዩነቱን በጽሑፍ ማስፈር ይችላል፣
5. ቅሬታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ቀደም ሲል ውሣኔ የሰጠ አባል በአጣሪ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ መገኘት የለበትም፡፡
6. አንድ አባል የራሱ፣ የሥጋ ዘመዱ፣ ወይም የጓደኛው ጉዳይ በሚታይበት ወቅት ይህንኑ ለኮሚቴው በማሳወቅ ከሰብሰባ መነሳት ይኖርበታል፡፡
7. በቀረበው ቅሬታ መሰረት ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ወይም በማሻሻል ውሳኔ ከሰጠ በስብሰባው ዕለት ተፈርሞ ተግባራዊ እንዲደረግ ይተላለፋል፡፡

## 55. የአባላት መብትና ግዴታ

ማንኛውም የኮሚቴ አባል፡-

1. እኩል ድምጽ የመስጠት፣
2. በስብሳበው ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣
3. የስብሰባውን ሥነ ሥርዓት ማክበር፣
4. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በስብሰባ ላይ ለመገኘት የማይችል ሲሆን አስቀድሞ ለስብሳቢው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 56. ውሣኔን እንደገና ስለማየት

ጉዳዩ በታየበት ወቅት ያልታየ ማስረጃ ሲቀርብ ወይም በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሲኖር ቀደም ሲል የተሰጠ ውሣኔ እንደገና እንዲታይ ይደረጋል፡፡

## 57. ውሣኔን ስለማስታወቅ

1. በቀረበው ቅሬታ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ ለአመልካቹ መግለፅ እና የገለጸው ሠራተኛ ስም ቀንና ፊርማ መስፈር ይኖርበታል፣
2. አመልካቹ ውሳኔው በጽሁፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ እንዲደርሰው ይደረጋል፣
3. ቅሬታ አቅራቢው በውሣኔው የማይስማማ ከሆነ በሥራ ሂደቱ፣ በሪጅን ጽ/ቤቱ ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችል መሆኑን ሊገለፅለት ይገባል፡፡

## 58. የኮሚቴው ሰብሳቢ ተግባር

1. ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፣
2. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው ተግባሩን በአግባቡ ስለመወጣቱ ይከታተላል፡፡
3. ስለ ሥራ አፈጻጸሙ ለዋና ዳይሬክተር ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 59. የኮሚቴው ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. የኮሚቴውን አጀንዳ በማዘጋጀት ለአባላቱ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
2. ቅሬታ የቀረበባቸው ጉዳዮች በተቀመጠላቸው ጊዜ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣
3. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ኮሚቴውን ይሰበስባል፣
4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 53(4) የተገለጸውን የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴውን የክንውን ሪፖርት እያዘጋጀ ለዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፡፡

## 60. ስለ መንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጽ/ቤት

1. ኤጀንሲው ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጽ/ቤት አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮ፣ የቢሮ ቁሳቁስ፣ አበል እና አስፈላጊ ሠራተኞች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

2. በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጽ/ቤት ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ተጠሪነታቸው ለኤጀንሲው የምዝገባና አበል ክፍያ ዳይሬክቶሬት ይሆናል፡፡

## ክ ፍ ል  አ ሥ ራ  ሁ ለ ት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 61. የመብት ግንኙነት

1. የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ከተቀጠረና ለጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተዳምሮ አበል ይወሰንለታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ሆኖም ወደ ስራ በመመለስ ለተፈጸመ አገልግሎት የሚከፈል አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ መብት አይኖርም፡፡

3. በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ/ 714/2003 (በአዋጅ ቁ/907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 52(2). መሠረት አንድ ባለመብት ሁለት የጡረታ መብት የሚያገኝበት ሁኔታ ሲኖር ሊያገኝ የሚገባውን አበል አይነትና መጠን በኤጀንሲው ዝርዝር አፈጻጸም ይወሰናል፣

### 62. ከሦስት ዓመት ባለነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተከልክሎ ስለነበረ የጡረታ አበል

1. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 ከመውጣቱ በፊት በፈፀመው /በፈጸመችው/ የወንጀል ጥፋት ምክንያት በፍርድ ቤት ከሦስት ዓመት ያላነሰ የፅኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት/የተወሰነባት፣

   ሀ. በመንግስት ሥራ ላይ የነበረና ከሃያ ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ፈጽሞ የጡረታ አበል የማግኘት መብት ያጣ የመንግስት ሠራተኛ፣

   ለ. ሲከፈለው የነበረው የአገልግሎት፣ የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት የጡረታ አበል ክፍያ የተቋረጠበት ባለመብት፣

   ሐ. የተተኪ የጡረታ አበል የተቋረጠበት ባለመብት

ከሐምሌ 1ቀን 2007ዓ.ም አንስቶ የዘለቄታ የጡረታ አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል/ይኖራታል፡፡

2. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የመንግስት ሠራተኛ የነበረና በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በፍ/ቤት ተረጋግጦ ከሦስት ዓመት ያላነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት ሆኖ፣

ሀ. ከሃምሌ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በኋላ በፈጸመው አገልግሎት ብቻ የዘለቄታ ወይም የዳረጎት አበል ተወስኖለት የነበረ የመንግስት ሠራተኛ የቀድሞ አገልግሎቱ ተደምሮ ተይዞ የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት የሚያስችለው ከሆነ ከሃምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ አበል ተሻሽሎ ይወሰንለታል፡፡

ለ. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ(ማሻሻያ)አዋጅ ቁጥር 907/2007 ጸንቶ በሥራ ላይ ከዋለበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ በሥራ ላይ ለሚገኝ ወይም ከዚህ በኋላ ለሚቀጠር የመንግስት ሠራተኛ ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት በመንግስት ሥራ ላይ ሆኖ የፈጸመው አገልግሎት ተዳምሮ ይታሰብለታል፡፡

## 63 ከሦስት ዓመት ባልነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት የተከለከለ የዘለቄታ የጡረታ አበል ክፍያ ለማግኘት ስለሚቻልበት ሁኔታ

1. በመንግስት ሥራ ላይ እያለ ወይም ከሥራ የተሰናበተ ሆኖ ከሃያ ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በተወሰነበት ከሦስት ዓመት ያለነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ምክንያት የጡረታ መብቱን ያጣ የመንግስት ሠራተኛ ፤

ሀ. ከሰኔ 1ቀን 1995 ዓ.ም በፊት በመንግስት ሥራ በፈጸመው አገልግሎት መነሻና መድረሻ የሚገልጽ በሚመለከተው የመንግስት የሥራ ኃላፊ የተፈረመ የጽሑፍ ማስረጃ፣

ለ. ባለጉዳዩ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎት የፈጸመ ከሆነ ከየመስሪያ ቤቶቹ በዚህ አንቀጽ (1)(ሀ) የተገለጸውን የጽሑፍ ማስረጃዎች፣

ሐ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(1) ለአገልግሎት ጡረታ አበል የሚቀርቡ ማስረጃዎችን፣

መ. ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ስለተወሰነበት ከሦስት ዓመት ያለነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ማስረጃ፣

ሠ. በመጨረሻ አገልግሎት ከፈጸመበት የመንግስት መ/ቤት የአገልግሎት መነሻና መድረሻ፣ ከሥራ ከመሰናበቱ በፊት የተከፈለ የ36 ወራት ደመወዝ የተሞላበት፣ የመስሪያ ቤቱ ማህተም የተደረገበት በኃላፊና በባለመብቱ የተፈረመ የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ.2፣

የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2. በተወሰነበት ከሦስት ዓመት ያለነሰ የእስራት ቅጣት ምክንያት ከሰኔ 1ቀን 1995 ዓ.ም በፊት በመንግስት መ/ቤት የፈጸመው አገልግሎት ተቀንሶ የዳረጎት አበል የተከፈለው የመንግስት ሠራተኛ የተቀነሰበት አገልግሎቱ ተደምሮ ሲታሰብ አግባብ ባለው የጡረታ አዋጅ ድንጋጌ የዘለቄታ የጡረታ አበል ለማግኘት የሚያስችለው መሆኑ ከተረጋገጠ የተከፈለውን የዳረጎት አበል በአንድ ጊዜ እንዲመልስ ተደርጎ አገልግሎቱ ተደምሮ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ የዘለቄታ የጡረታ አበል ይወሰንለታል፡፡

3. በፈጸመው የወንጀል ጥፋት ምክንያት በፍ/ቤት ከሦስት ዓመት ያለነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኖበት የጡረታ መብቱን ያጣ የመንግስት ሠራተኛ ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም እና ከዚያ በኋላ የፈጸመው አገልግሎት ተደምሮ ሲታሰብ ከሃያ ዓመት ያነሰና አግባብ ባለው የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት የዘለቄታ የጡረታ አበል ለማግኘት የማያስችለው ከሆነ ለመንግስት ሠራተኛ ወይም ለተተኪዎቹ የሚከፈል የዳረጎት አበል ወይም የመዋጮ ተመላሽ አይኖርም፡፡

4. በፈጸመው የወንጀል ድርጊት በፍ/ቤት ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ ከሦስት ዓመት ያለነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት ስለተወሰነበት ሲከፈል የነበረው የጡረታ አበል የቀረበት(የተቋረጠበት)ባለመብት(ተተኪን ይጨምራል)ከሆነ፣

ሀ. የጡረታ አበል ሲቀበልበት የነበረ መታወቂያ፣የክፍያ መቆጣጠሪያ/ፔይ ቡክ/በእጁ ካለ፣

ለ. የጡረታ አበል እንዲከፈለው ከመጠየቂያ ማመልከቻ ጋር በቅርብ ጊዜ ከተነሱት 4X3 ፎቶግራፍ፣

ሐ. በማመልከቻው ላይ የጡረተኛ መለያ ቁጥርና የጡረታ አበሉን ለመቀበል የሚፈልጉበትን የክፍያ አድራሻ በመጥቀስ፣

መ. ተተኪ ከሆኑ አግባብ ባለው ፍ/ቤት የተሰጠውን የተተኪነት ማስረጃ፣

በመያዝና በአካል በመቅረብ ለኤጀንሲው ዋና መ/ቤት ወይም ለሚቀርባቸው የኤጀንሲው ሪጅን ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመቅረብ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

5. የአገልግሎት፣ የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ዘለቄታ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ እያለ ወይም አገልግሎቱ ለዘለቄታ ጡረታ አበል ብቁ የሚያደርገው የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እሥራት ቅጣት ስለተወሰነበት የጡረታ መብት ያልተሰጠው የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 907/2007 ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ባለመብት ተተኪዎች አዋጁ ከፀደቀበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ለወደፊት ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ሊወሰን ይችላል፡፡
6. በጽኑ እስራት ምክንያት መብታቸውን አጥተው ለቆዩ ባለመብቶችና ተተኪዎች ማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 ላይ የተመለከተው ማስረጃ ሲቀርብ በቅድሚያ የሟች የአገልግሎት ዘመን ለዘለቄታ ጡረታ አበል የሚያበቃው ስለመሆኑና ስለተተኪዎቹ ማንነትና አግባብነት ተጣርቶ ተገቢው ይወሰናል ፡፡

## 64 የወላጅ ጡረታ አበል አከፋፈል

1. ለእያንዳንዳቸው የወር ገቢ/ የጡረታ አበልን ይጨምራል እስከ ብር1,000.00/ አንድ ሺህ ብር/ የሚያገኙ ወላጆች ሟች ልጃቸው በሕይወት በነበረ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሚያደርግላቸው ድጋፍ ይተዳደሩ የነበረ ለመሆኑ በአሠሪ መሥሪያ ቤት፣ በፍ/ቤት፣ በወረዳ ወይም በቀበሌ አስተዳደር ተረጋግጦ ማስረጃ ከቀረበለት እያንዳንዱ ወላጅ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡
2. በየወሩ የሚከፈል የጡረታ አበልን ጨምሮ የእያንዳንዳቸው የወር ገቢ ከብር 1000 (አንድ ሺህ) ያላነሰ ገቢ ያላቸው ወላጆች ግን ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተገለጸው በተጨማሪ ተቆራጩን ገንዘብ ከተቀበሉበት መሥሪያ ቤት የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 65 ስለጡረተኞች ቆጠራ

የጡረተኞችን ብዛትና የሚከፈለውን የአበል መጠን ለማወቅ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ይካሄዳል:: አፈጻጸሙ በኤጀንሲው በሚወጣ ዝርዝር አፈጻጸም ይወሰናል::

## 66 የመመሪያው የመሸጋገሪያ ተፈጻሚነት

በዚህ መመሪያ እንዲታይ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለተፈጠሩ ሕጋዊ ጉዳዮች ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

## 67 ስለተሻሩ መመሪያዎችና አሠራሮች

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን አሰራር ወይም ልምድ በዚህ መመሪያ በተገለጹ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

## 68. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም አንስቶ የፀና ይሆናል::

የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

ዳባ አርያ
ዋና ዳይሬክተር